**ዮም፡ አሚሩ ለመስከረም፡ ዕለተ ፍሥሓ ኮነ!**
**በእንተ በዓለ ልደታ፡ ለድንግል ማርያም!**
**ወበእንተ በዓለ ልደቱ፡ ለኢየሱስ መሢሕ!**

**ዛሬ፡ መስከረም አንድ ቀን፡ የደስታ ዕለት ኾነ!**
**የድንግል ማርያም፡ የልደቷ በዓል ነውና!**
**የልጇም፡ የኢየሱስ መሢሕ፡ የልደቱ በዓል ነውና!**

ይድረስ፦ ለኪዳናዊ ወንድሜ ፈቃደ-ሥላሴ ገብረ-ክርስቶስ!

በያለንበት ለሚጠብቁንና ለሚመግቡን፥ ለሚመሩንና ለሚንከባከቡን፡ በሰማያት ለሚኖሩት አባታችንና እናታችን፡ የማያቋርጠው ምስጋናችን ይድረሳቸውና፡ በመለኮታዊው ጸጋና በረከት፡ በኪዳናውያትና በኪዳናውያን የኢትዮጵያ ልጆች፡ ፍሬያማ ከኾነው ቤተሰብህ ጋር፡ በመልካም ኹኔታ እንደምትገኙ፥ የዓውደ ዓመቱንም በዓል፡ በሓሤት መንፈስ እያከበራችሁ እንዳላችሁ አምናለሁ።

"ማኅበረ ሥላሴ፡ ዘደቂቀ ኤልያስ" በሚል ስያሜ እየተንቀሳቀሰ ያለውን ሃይማኖታዊ ድርጅት በሚመለከት፡ በነሓሴ ፲፯ ቀን ፳፻፯ ዓ. ም. ጽፈህና አንድ ዐባሪ የድምፅ ሸክላን ጨምረህ፡ እቤት ድረስ አምጥተህ፡ እንዳገኘው ስላደረግኸው ደብዳቤህ፡ ምንም እንኳ፡ የመድረሱ ዜናና የምርቃቱ መልእክት፡ ወዲያው፡ በኪዳናዊት ስብከተ ኤርምያስ በኩል፡ በስልክ የተላለፈልህ መኾኑን ባውቅም፡ አኹን ደግሞ እንደገና፡ በዚህ አጋጣሚ፡ በጣሙን "እግዜር ይስጥልኝ!" ልልህ እወድዳለሁ።

የደብዳቤህን መልእክት ካነበብሁትና የሸክላውን ጥንቅር ካዳመጥሁት በኋላ፡ በአንተ በኩል፡ ዝግጅቱን፡ በዚህ መልክ አቀናብረህና ከውነህ፡ እንዲደርሰኝ በማድረግህ፡ አንተን፡ በዚህ አሳቢነትህና ድካምህ አድንቄ ካሞገስሁህ በኋላ፡ በዚህ የመንፈስ ኃይል አነሣሥቶና አነቃቅቶ፡ አዎን! ለዚህ፡ በእግዚአብሔር እውነት ለተቃኘው፡ የጣፋጭ ፍሬ አሳብና አስተያየት አብቅቶ ደብዳቤውን በማጽጻፍ ያስፈጸመህን፡ መንፈስ ቅዱስን፡ እንደተለመደው አመስግኛለሁ።

ከላይ የተጠቀሰውን፡ ይህን ሃይማኖታዊ ድርጅት በሚመለከት የላክህልኝ መረጃ፡ ለእኔ እንግዳ ነገር አልኾነም፤ ምክንያቱም፡ ቀደም ብሎ፡ በተለያየ መልክ እየደረሰኝና እያወቅሁት ስከታተለው የቆየሁ በመኾኑ ነው። በጎዋ ሰሌዳችን፥ በፌስቡክ የጥያቄና መልስ መድረካችንም አማካይነት ተጻጽፈንበት እንደነበረ፡ ታስታውሰው ይኾናል።

የዚህ እንቅስቃሴ ቀንደኛ አባሎችና መሪዎች፡ እየራሳቸውን፡ "ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት ነን!" የሚሉ፡ እውነተኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ቢኾኑ ኖሮ፡ በእነዚያ በተለዋወጥናቸው ደብዳቤዎች አማካይነት፡ **የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር *መንግሥት ልጆችና ዜጎች፥ ወራሾችና አገልጋዮች ካህናት*** **ኾነው፡** ከእርሷ የተቀበሉትን መለኮታዊ ተልእኮ፡ ከእኛ ጋር በአንድነት ሊያካኺዱ በመረጡና በቻሉም ነበር። ንገር ግን፡ ባለመኾናቸውና ባለመፈለጋቸው፡ ሳይቻላቸው ቀርቶ፡ የራሳቸውን ባዕድና ተቃራኒ መንገድ ተከትለው፡ ይኸው፡ በባዕዳን የጥፋት መሣሪያነታቸው ቀጥለውበት ይገኛሉ።

እንደሌሎቹ ተመሳሳይ ማኅበሮችና ድርጅቶች ኹሉ፡ ይኼም የእነዚህ ሰዎች እንቅስቃሴ፡ በቀጥታ፡ ሲካኼድ የቆየውን፡ የባዕዳንን፥ በተለይም፡ የይሁድናን ዓለም-ዐቀፍ መሠሪ ዓላማ፡ ከግብ ለማድረስ፥ ምቹና ቀልጣፋ መሣሪያ በመኾን፡ በገንዘብና በዘመናዊው ፈሊጥ፥ በጥበብና በኃይልም እየታገዘ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥት* ላይ፡** ተፃራሪ ኾኖ፡ በገሃድ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በረቂቅ የተቃውሞ፥ የአፍራሽነትና የአጥቂነት ስልት እንዲሠራ፡ ኾነ ተብሎ፡ በጥናትና በዕቅድ የተፈጠረ፥ በከባድ ይዞታም እየተካኼደ ያለ፡ የክፋት ሰዎች፡ አንዱ፡ የወረራ ዘመቻ ዘርፍ መኾኑን ልታውቀው ያስፈልጋል።

እዚህ ላይ፡ ይህንኑ ርእሰ ጉዳይ በሚመለከት፡ ፩. ከዚሁ እንቅስቃሴ፡ ቀንደኛ አባሎችና መሪዎች መካከል፡ አንዱ ከኾኑት ሰው፡ በፌስቡክ ላይ፡ በተቃውሞና በነቀፌታ ለተጻፈልኝ ጦማር፡ የሰጠሁትን ምላሽ፣ ፪. በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፣ በስድስተኛው የቃለ-ዐውዲ፡ ዐዋጅ ውስጥ፡ አግባብነት ያለውን ተጠቃሽ ክፍል፡ ለዝክረ ነገርና ለዓይነት ያህል አቅርቤልሃለሁ።

<u>የመጀመሪያው፡</u> ይህ ነው፡- ይድረስ፡- ለአባ ዳንኤል ተሜነ አግዜ! *<u>"ከንቡረ እድ ኤርሚያስ ከበደ ለተሰጠው መልስ እኔ አባ ዳንኤል ተሜነ አግዜ የምሰጣቸው መልስ ይህ ነው፡፡"</u>* በሚል ርእስ፡ በኅዳር ፩ ቀን፥ ፳፻፲ ዓ. ም. በፌስቡክ የጎዋ መድረካችን ላይ የጻፉልኝን የመልስ ደብዳቤዎን አግኝቼ አነበብሁት። እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

ይህን መልስ እንድሰጥ ያስፈለገኝ፡ በይበልጥ፡ አንባቢዎቻችን፡ እውነቱን ይረዱት ዘንድ፡ ለእነርሱ ስል ነው። እርስዎማ፡ እግዚአብሔር፡ በጥንተ ተፈጥሮ፡ በውስጥዎ ካኖረው፡ ኅሊናዎ የተነሣ፡ ያችን የእግዚአብሔርን እውነት አውቀዋት እያሉ፡ ነገር ግን፡ ሊቀበሏት ባለመፈለግዎ ብቻ፡ በተቃውሞ፡ ከራስዎ አርቀዋታልና፡ ላይሰሙ፥ ላይቀበሉ፡ ለእርስዎ መጻፉ፡ እምብዛም ጠቃሚ መስሎ አልታየኝም።

ይኹን እንጂ፡ በዚሁ፡ በተቃውሞ ጽሑፍዎ ውስጥ ከዘረዘሩዋቸው ነገሮች መካከል፡ የእኔ መልስ የሚያስፈልጋቸው መስለው ለታዩኝ ብቻ፡ ከዚህ የሚከተለውን መግለጫ ሰጥቻለሁ፡-

፩ኛ፡ ስምዎንና ትክክለኛ ማንነትዎን በሚመለከት ለሠነዘሩዋቸው፥ ወቀሳና ዘለፋ ለተመላባቸው ኃይላተ ቃላት፡ የምመልስልዎ፡ ይህ ነው፡- ለእኔ፡ ቍም ነገሩ፡ የእርስዎ "አባ ዳንኤል ተጫነ አግዜ"፥ ወይም፡ "አባ ወልደ አረጋዊ ዓምደ ሥላሴ" መባል፥ ወይም፡ መኾን አይደለም፤ ምክንያቱም፡ በእነዚህ ኾነ፡ በሌሎች የተለያዩ በርካታ ስሞች ቢጠሩ፡ የእርስዎን ምንነትና ማንነት፡ ማለትም፡ የተፈጥሮ አካልዎና ባሕርይዎ፡ በምንም መልክና ይዘት፡ ሊቀየር፥ ወይም፡ ሊለወጥ፡ ፈጽሞ የማይችል በመኾኑ ነው።

ያውም ቢኾን፡ እነዚህን ኹለት ስሞች የሰጡን፡ እርስዎ መኾንዎን፡ ራስዎ በጻፏቸው ደብዳቤዎች፡ በበቂ ማስረጃ ለማረጋገጥ የሚቻል ከመኾኑ ጋር፡ አንባቢዎቻችንም፡ እየራሳቸው የሚያውቁት በመኾኑ፡ ለእርስዎ፡ ራስዎን፡ "መነኵሴ ነኝ!" ለሚሉት ሰው፡ በእነርሱም ዘንድ የሚተርፍዎ፡ ትዝብት ብቻ እንጂ፡ ማንም ሰው፥ እኔ ጭምር፡ ለዚህ፡ ለማይረባ ነገር፡ ጊዜውንና የአእምሮ ኃይሉን ሊያባክን የሚፈልግ ሰነፍ ሰው እንኳ፡ የሚኖር አይመስለኝም። እርስዎም ቢኾኑ፡ ለዚህ ፍሬቢስና ከንቱ ለኾነ ነገር፡ ይህን ያህል መድከምና መቀባጠር ባላስፈለገዎ ነበር።

እንደማንም ሰው፡ "ዳንኤል ተጫነ አግዜ" የዓለም ስምዎ፥ "ወልደ-አረጋዊ ዓምደ-ሥላሴ" ደግሞ፡ የክርስትና፥ ወይም፡ የምንኵስና መጠሪያዎ መኾኑን ቢገልጡ፡ ምን ይጎዳዎት ነበር? "እውነቱ፡ ይህ ነው!" ቢሉስ፡ ምን ነውር ነበረበት? ይህ ኹሉ፡ የሚቻልና ቀላል ኾኖ ሣለ፡ ነገር ግን፡ ባለመታደል፡ ሳይኾን ቀርቷል።

፪ኛ፡- እንዲህ የኾኑት፡ ያለምክንያት እንዳይደለ፡ ለማንም ግልጽ ኾኗል፤ ከዚህ፡ የመልስ ደብዳቤዎ፡ በእኔ በኩል፡ የተገነዘብሁት ነገር ቢኖር፡ በከፍተኛ ቁጣና ንዴት የተመሉ ኾነው፡ በጦር እንደቆሰለ ኃይለኛ ዐውሬ፡ እንዲህ ያወራጪዎ፡ ከራስዎ ድብቅ ምንነትና ማንነት ጋር፡ ሌላ፡ አንዳች የተሠወረ ዓላማ እንዳለ፥ ያም፡ በመንፈስ ቅዱስ ረቂቅ ግብር ስለተከሠተብዎት መኾኑ፡ የመልስ ደብዳቤዎ አጻጻፍ መልክና ይዘት፡ አጋልጦ መስክሮብዎታል።

እንዲህ ካልኾነ፡ ታዲያ! ቀድሞውኑ፡ ራስዎንና የማን ወገን መኾንዎን፡ እንዲህ፡ እንዳኹኑ፡ ለምን ሳይገልጡልኝ ቀሩ? ማለትም፡ ቀጥዬ ላወሳው ስለፈለግሁት፡ እርስዎም፡ "ቴዎድሮሳችን ነው!" ስላሉት፤ ስለቅዱስ ኤልያስና "መንግሥተ ሥላሴ ዘደቂቀ ኤልያስ" ስለተባለው ማኅበር አባልነትዎ፥ ወይም፡ ባልደረብነትዎ፡ በጥቆማ መንገድ እንኳ፡ ለምን ሳያሳውቁኝ ቀሩ?

አኹን ግን፡ ትክክለኛ ማንነትዎንና የማን ወገን መኾንዎን አረጋግጠው አሳወቁ! እውነተኛ ዐምሓራ፥ ክርስቲያን፥ እና/ወይም፡ ኢትዮጵያዊ ሳይኾኑ፡ ይሁዲነትዎን፥ ከዚህ የተነሣም፡ በኢትዮጵያ እና በልጆቿ ላይ፡ ሲያካኺዱ የኖሩትን፥ አኹንም እያካኺዱ ያሉትን የጥፋት ዓላማ፡ ለመፈጸምና ለማስፈጸም፡ የእነርሱ አገልጋይ ጭፍራ መኾንዎን በይፋ መሰከሩ።

ታዲያ! "ቀዳሚትና የአይሁድ" በተባለችው፡ በሰባተኛዪቱ ቀን ሰንበትነት ብቻ፥ እንዲሁም፡ በትስብእት ሰውነት ኾነ፥ በመንፈስ ቅዱስነት መጥቶ፡ የእናቱ፡ የቅድስት ድንግል ማርያም በኾነችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥቱ፡ በሰማይና በምድር ፍጥረታተ ዓለማቱ ላይ፡ በነፍስና በሥጋ፥ በመንፈስም፥ በካህን ሊቀ ካህናትነት ኾነ፥ በንጉሥ ንጉሥ ነገሥትነት ሰፍኖ፡ እየመራና እያስተዳደረ ያለው፡ የኢትዮጵያዊው የኢየሱስ መሢሕነት ቀርቶ፡ ስለቅዱስ ኤልያስ መምጣት ብቻ፡ ይህን ያህል የሚያብሰከስክዎ፡ ከቶ፡ ምክንያቱ፡ ምንድር ነው? "ይሁዲነት" የሚባለው እምነትና ማንነት፡ ምንድር መሰለዎ? ይህ አይደለምን? ነው እኮ!

ስለቅዱስ ኤልያስማ፡ ስንት ጊዜ ተነገረ? እልፍ አእላፋት ጊዜ አልተነገረምን? እውነተኛ ዐምሓራ፥ እውነተኛ ክርስቲያን፥ እና/ወይም፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ቢኾኑ ኖሮ፡ አይሁድ ሰቅለው የገደሉት፡ ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ በዘመኑ ለነበሩት አይሁድ የተናገረውን መለኮታዊ ቃል፡ አምኖ ለመቀበል፡ የኹለት ሺህ ሰባት ዓመታት ዕድሜ አይበቃዎትም ነበርን? በእርግጥ ይበቃ ነበር። ነገር ግን ባለመታደል አልኾነም።

ያም፡ መለኮታዊ ቃል፡ "ወበጺሖ እግዚእ ኢየሱስ፡ ብሔረ ቂሣርያ ዘፊልጶስ፡ ተስእሎሙ ለአርዳኢሁ፡ እንዘ ይብል፡ 'መኑ ይብልዎ ሰብእ፡ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው?' ወይቤልዎ፡ 'ቦ እለ ይብሉከ፡ ‹ዮሓንስሃ መጥምቀ!› ወካልአን ይብሉከ፡ ‹ኤልያስሃ!› ወመንፈቆሙ ይብሉከ፡ ‹ኤርምያስሃ! ወእመ አኮ፡ አሓዱ፡ እምነቢያት ቀደምት!› ወይቤሎሙ፡ 'አንትሙኬ፡ መኑ ትብሉኒ?' ወአውሥአ፡ ስምዖን ጴጥሮስ፤ ወይቤ፡ 'አንተ ውእቱ፡ ክርስቶስ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው!'

ማለትም፡ "ጌታችን ኢየሱስም፡ የፊልጶስ አገር ወደምትኾን፡ ወደቂሣርያ ከተማ በደረሰ ጊዜ፡ ደቀ መዛሙርቱን፡ 'ሰዎች፡ የማርያምን ልጅ [እኔን] ማን ይሉታል?' ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፡ ‹'ዮሓንስ መጥምቅ ነህ!' የሚሉህ አሉ፤ ሌሎችም፡ 'ኤልያስ ነው!' ይሉሃል፤ እኩሎቹም፡ 'ኤርምያስ ነው!' ይሉሃል፤ ያም ባይኾን፡ 'ከቀደሙት ነቢያት፡ አንዱ ነው!' ይሉሃል፤› አሉት። እርሱም፡ 'እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ?' አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም፡ መልሶ፡ 'አንተ፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!' አለው።" የሚለው ነው።

እንግዴህ፡ እርስዎ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፥ እውነተኛ ዐምሓራ፥ እውነተኛ ክርስቲያን ቢኾኑ ኖሮ፡ ሓዋርያቱ፡ በዚህ መልሳቸው ውስጥ፡ በስም ለይተው የጠቀሷቸው ነቢያት፡ መጥምቁ ዮሓንስ፥ ኤልያስና ኤርምያስ ሲኾኑ፡ በጊዜው፡ በአካለ ሥጋ፡ ዐብሮአቸው የነበረው መጥምቁ ዮሓንስ፡ በኤልያስ መንፈስ የመጣ መኾኑን፡ ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ "ወእመሰ ትፈቅዱ ትትወከፍዎ፡ ዝ ውእቱ ኤልያስ፡ ዘሀለዎ ይምጻእ፤ ዘቦ ዕዝን፡ ሰሚዐ ለይስማዕ!

ማለትም፡ "ልትቀበሉትስ ብትወድዱ፡ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ፡ ይህ ነው። የሚሰማ ጆሮ ያለው፡ ይስማ!" ብሎ በተናገራቸው ቃሉ፡ የኤልያስን፡ በመጥምቁ ዮሐንስ ሰውነት ተገልጾ መምጣት እንዳረጋገጠላቸው ያውቃሉ።

ከዚያ በኋላም፡ በደብረ ታቦር ላይ፡ ኤልያስን፡ ከሙሴ ጋር አይተውት፡ ከተራራው ሲወርዱ፡ "እፎ ይብሉ ጸሓፍት፡ 'ሀለዎ ይምጻእ ኤልያስ ቅድመ'።

ማለትም፡ "እንግዴህ፡ ጻፎች! 'ኤልያስ፡ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል!' ስለምን ይላሉ?" ብለው በጠየቁት ጊዜ፡ ጌታችን መሢሕ ኢየሱስ፡ መልሶ፡ "እወ! ኤልያስ፡ ይቀድም መጺአ፤ ወያስተራትዕ ኵሎ። ወእብለክሙ ባሕቱ፡ ከመ ኤልያስ፡ ወድአ መጽአ፤ ወኢያእመርዎ፤ ወባሕቱ፡ ገብሩ ላዕሌሁ፡ ኵሎ፡ ዘከመ ፈቀዱ።

ማለትም፡ "ኤልያስማ፡ አስቀድሞ ይመጣል፤ ኹሉንም ያቀናል፤ ነገር ግን፡ እላችኋለሁ፡- ኤልያስ፡ ከዚህ በፊት መጣ፤ የወደዱትንም ኹሉ አደረጉበት እንጂ፡ አላወቁትም።" አላቸው። (ማቴ. ፲፩፥ ፲፬፤ ፲፯፥ ፩-፲፫።)

ታዲያ! ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ በዘመኑ ለነበሩት አይሁድ፡ እንዲህ አብራርቶ የነገራቸውንና አስረግጦ ያመለከታቸውን እውነታ ለመረዳትና ለማመን፡ አለመቻል ብቻ ሳይኾን፡ የበለጠ ባስተማራቸውና በገለጠላቸው መጠን፡ በዓይናቸው የሚያዩትን እውነት በመቀበል ፋንታ፡ እንደገና በባሰ ኹኔታ፡ እየጠሉትና እየተቃወሙት ኼደው፡ በመጨረሻ ሰቅለው እስከመግደል መድረሳቸው፡ ይሁዲነት ምን እንደኾነ፡ ማሳወቃቸው አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ። ይህ ኹኔታ፡ ዛሬ ባሉት ጭምር፡ ይኸው እየታየ አይደለምን? አዎን! እየታየ ነው።

እነዚያ የቀድሞዎቹ አይሁድ ያሉት፥ እነዚህ፡ የዛሬዎቹም አይሁድ የሚሉት፡ ምንድር እንደሚሉ፡ እርስዎ፡ ምንም ምን ይኹኑ፡ ያውቁ የለም እንዴ!? "የለም! በመጀመሪያ፡ ከፍጥረተ ዓለም በፊት፡ በመለኮትነት፥ በመጨረሻም፡ ከፍጥረተ ዓለም በኋላ፡ በሰውነት፡ ከእግዚአብሔርና ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል ማርያም የተወለደው፡ አንድያ ልጃቸው የኾነው ኢየሱስ፡ የእግዚአብሔር ልጅም፥ እውነተኛው መሢሕም አይደለም! እውነተኛው መሢሕ፡ ኤልያስን አስቀድሞ፡ ገና ወደፊት ይመጣል!" አይደለም እንዴ ያሉትና የሚሉት!?

ታዲያ! ዛሬ፡ እርስዎና መሰሎችዎ፡ ያለአንዳች ውልውልና ጥርጥር የምትሉት፡ ይህንኑ አይደለም እንዴ!? ይሁድና፥ ወይም፡ ይሁዲነት እኮ፡ ይኼ ነው። እስካኹን፡ ያላወቁት ከኾነ፡ እንግዴህ ወዲህ ይወቁት!

ቀደም ብሎ፡ እውነተኛውን ይሁዲነት፥ ወይም እስራኤላዊነት፡ ኋላም አከታትሎ፡ እውነተኛውን ክርስትና ተቀብሎና አስተናግዶ ያዋሓደው ኢትዮጵያዊነት ግን፡ እንዲህ አይደለም።

ኢትዮጵያዊነት፡ ጥንቱንም በመሠረቱ፥ ባሳለፈውም የህልውና ዘመኑ፥ ዛሬም በሚገኝበት ሕያውነቱ፥ ወደፊትም በሚቀጥልበት ዘለዓለማዊነቱ፡ እንዲህ፡ እናንተ የምትሉትን ይሁዲነትን የሚመስል፥ በዚህ ይሁዲነትም፡ የምታደርጉትን የሚያደርግ አይደለም። ኢትዮጵያዊነት፡ ከዚህ፡ የይሁዲነት አካልና ባሕርይ፡ ፈጽሞ የራቀና የተለየ፥ ተቃራኒው የኾነ አካልና ባሕርይም ያለው ኾኖ፡ የነፍስ የኾነውን፡ ኪዳነ ልቡናን፥ የሥጋ የኾነውን፡ ኪዳነ ኦሪትን እና የመንፈስ የኾነውን፡ ኪዳነ ምሕረትን፡ በምሥጢረ ሥላሴ፡ አንድ አድርጎና አስማምቶ ያዋሐደ እምነትና ህልውና ነው።

እርስዎና መሰሎችዎ የተማፀናችሁት ይሁዲነት፡ ሰዎች፡ በገዛ ዓይናቸው እያዩትና እየተመለከቱት፥ በገዛ ጆሮአቸው እየሰሙትና እያዳመጡት፥ በገዛ እጃቸው እየዳሰሱትና እየጨበጡት፥ በገዛ አፍንጫቸው እየተነፈሱትና እያሸተቱት፥ በገዛ ምላሳቸውም፡ እየቀመሱትና እያጣጣሙት ያለውን ነገር፡ "አዎን! ይህ ነገር፡ በእውን እየኾነ ያለ፡ እውነት ነው!" ብለው፡ ሊቀበሉትና ሊያምኑት ያላስቻለ ሕፁፅ ሲኾን፡ ኢትዮጵያዊነት ግን፡ ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ "ብፁዓንሰ፡ እለ እንዘ ኢይሬእዩኒ፡ የአምኑኒ!"

ማለትም፡ "ብፁዓንስ፡ ሳያዩኝ፡ የሚያምኑብኝ ናቸው!" ብሎ ለተናገረው መለኮታዊ ቃል ያበቃ፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። (ዮሓ. ፳፥ ፳፱።)

ይህን፡ የጌታችንን የኢየሱስ መሢሕን ቃል፡ ሕይወታቸው አድርገው የኖሩት፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ብቻ መኾናቸውን፡ ለመላው የዓለም ሕዝቦች ሊያሳውቅ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በዚያ፡ "የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ" በተባለው፡ ኢትዮጵያዊ ሰውነት ላይ የታየውን፡ የሃይማኖትና የምግባር ፍጹም ብቅዓት፡ አብነትና አርአያ አድርጎ ከሥቶ አቅርቦታል። ያም የሃይማኖት ሰው፡ የኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሕንደኬ፡ ጃንደረባዋ፡ ማለትም፡ ባለሟሏና የገንዘብ ምሉኳ የነበረው ኢትዮጵያዊ እንደኾነ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቦ ይነበባል። (የሓዋ. ፰፥ ፳፮-፴፱።)

ስለዚህ፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት ኹላችሁ፡ በዚህ፡ ያለማመን ግትርነታችሁና አንገተ ደንዳናነታችሁ እያረጋገጣችሁ ያላችሁት፡ ይሁዲነትን እንጂ፡ ኢትዮጵያዊነትን አለመኾኑን፡ በጽሑፍዎ አስመስክራችኋል።

እንዲያው ለመኾኑ፡ እርስዎ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፥ እውነተኛ ዐምሓራ፥ እውነተኛ ክርስቲያን ከኾኑ፡ "'ቴዎድሮስ ነው!' ከሚሉት፡ ከቅዱስ ኤልያስ እና ከኢየሱስ መሢሕ፡ ማንኛው ይበልጣል?" ብዬ ብጠይቅዎ፡ መልስዎ፡ ምን ይኾናል? በእርስዎ አጻጻፍ እንደሚታየው ግን፡ ቴዎድሮስን፥ ወይም ቅዱስ ኤልያስን ያስበለጡ ኾነው ተገኝተዋል።

*"ተዋሕዶን፣ አንዷቷን ዕለተ ሰንበትንና ሕግ እና ነቢያትን አውጇ፡፡"* በማለት፡ ስለኦሪታውያኑ አይሁድ እንጂ፡ "ወንጌል" ስለሚባለው፡ ስለአዲስ ኪዳኑ የምሥራች ቃል፡ አንድም ጊዜ፥ ወይም፡ አንድም ቦታ አልተናገሩም።

ስለዚህ፡ ስለእርስዎ ምንነትና ማንነት፡ ማለትም፡ እርስዎ፡ ዓይነተኛው ይሁዲ ስለመኾንዎ፥ እንደዚያም ካልኾኑ፡ የእነርሱ አገልጋይ ስለመኾንዎ፡ ከላይ፡ ቀደም ብሎ የተነገረው ኹሉ፡ እውነት መኾኑ፡ በዚህ ድርጊትዎ ይረጋገጣል።

ወደፊት፡ ወደዓለም መጥቶ፡ ከዓለሙ ጋር የሚፋረድ፡ እርስዎ እንዳሉት፡ ቅዱስ ኤልያስ ሳይኾን፡ ኢትዮጵያ፡ እርሷም፡ ራሷ ድንግል ማርያም መኾኗን፡ ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ እንዲህ ሲል የተናገረው፥ ባለፈው ጽሑፌም የተጠቀሰው መለኮታዊ ቃል፡ ያረጋግጣል፡-

**"ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ፡ አመ ዕለተ ደይን፡ ምስለ ዛ ትውልድ፤ ወትትፋትሓ፥ ወታስተኃፍራ፤ እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር፡ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን፤ ወናሁ፡ ዘየዐቢ እምሰሎሞን፡ ሀሎ ዝየ።**

ማለትም፡ **"ንግሥተ አዜብ (ኢትዮጵያ)፡ በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ፡ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም። የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና። እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።"** (ማቴ. ፲፪፥ ፵፪።)

፫ኛ፡ እኔን፡ ወደኢትዮጵያ እንድመለስ፡ ከዚህ በታች በሠፈሩት የይፋ ደብዳቤዎችዎ፡ ያን ያህል የወተወቱኝና የተማፀኑኝ፡ ለምን ኖርዋል? ለዚሁ ኤልያሳዊ ዓላማችሁ አፈጻጸምና ከግብ መድረስ፡ ዐባሪ ተባባሪና ግብረ-ዐበር እንድኾናችሁ ኖርዋልን? እየራሳቸው፡ ለእየራሳቸው እንዲበይኑ፡ እነዚህን ደብዳቤዎችዎን፥ እኔም፡ ለእነርሱ የሰጠሁዎትን መልሶች፡ አንባቢዎቻችን ይመለከቷቸው ዘንድ፡ እነሆ አቅርቤያቸዋለሁ፡-

<u>የአባ ዳንኤል ተጫነ ደብዳቤ፡-</u>

ሀ. *"በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን፤ የተከበሩ ውድ አባት ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ስለመልስዎ አመሰግናለሁ ይህን ሁሉ መዘብዘቤ ከፍቅር ነው አባቴ ማንነትዎን ስላወኩ ደግሞም በዚህ ልዩ ሰአት የእርስዎን እዛ መቀመጥ ነፍሴ ጠላችው አላውቅም ደግሞ እግዚአብሄር እንደጠራዎት አውቃለሁ ወዳገርዎ እንዲገቡ ብዙ ጥሪዎች ባንድም በሌላም ደርስዎታል ይረዱት አይረዱት አላውቅም ደግሞም እኔ የማላቀው እንዲቆዩ የተሰጥዎት የእግዚአብሔር ድምጽ ካለ እሱ ይበልጣልና ይቆዩ ከመመኪያዎ ድንግል ማርያም ግን የደረስዎ መልእክት ከሌለ ግን እባክዎ እሷን ቢጠይቁ አንድ የማውቀው እውነት አለና ነው ለማንኛውም የኢትዮጵያ አምላክ አገርዎ ገብተው ያሳየኝ በጣም አከብርዎታለሁ ሰላም ይሁኑ!"*

**የእኔ መልስ፡-**

"በመጨረሻ ስለጻፉልኝ እ-ጦማርና በውስጡ ስላሠፈሯቸው የመንፈስ ቅዱስ ቃላት፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ! ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በቅርቡ፡ በታወጀው በ፩ኛውና በ፪ኛው ቃለ ዐዋዲ መሠረት፡ እርስዎም፥ እኔም፡ ከመጀመሪያው፥ ከመካከለኛውና ከመጨረሻው መልከ ጼዴቆች ላገኘናቸው ሕያዋን የቃል ኪዳን ጸጋና በረከት፥ ሥልጣንና ክብር፡ እርስዎም፡ እንደእኔ፡ ራስዎን፡ ለዚህ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ዐብቅተው ከኾነ፡ እንግዴህ ወዲህ የምጠራዎ፡ "ኪዳናዊ ወልደ-አረጋዊ!" ብዬ መኾኑን እንዲያውቁት ይኹን!

"ይህም የሚኾነው፡ በዚሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትዎ፡ ከዚያ መልከ ጼዴቅያዊ ጸጋና በረከት፥ ሥልጣንና ክብር የተነሣ፡ በዕድሜም ኾነ በማዕርግ፡ ከአሪታውያኑ የአይሁድ እርሾ ትምህርትና ከኦርቶዶክሳውያኑ የግብፅ ምንኵስና ቀኖና ይልቅ፡ በ፩ሺ ፰፻ እና በ፪ሺ ዓመታት ዕድሜ የሚቀድመውንና የሚበልጠውን፡ የኢትዮጵያውያኑን ቅዱስ ኪዳናዊ የእግዚአብሔርን ልጅነት፥ ካህንነትና ነጋሢነት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ በዘለዓለማዊነት ስለተቀዳጁት ነው።

"በእኔም በኩል፡ ከዚህ ቀደም እንደጻፍሁልዎ፡ በጥንቃቄ ጠብቀን ልንፈጽመው በሚገባን፡ በመለኮታዊው መመሪያ ቃል መሠረት፡ እኔ፡ በቅዱሱ ኪዳን አገልግሎት፡ ወንድምዎ ስለኾንሁ፥ የእርስዎና የእኔ፥ የኹላችንም አባት ግን፡ አንዱ እርሱ፡ የሰማዩ ብቻ ስለኾነ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እርስዎ፡ እኔን ሊጠሩኝ የሚገባዎ፡ "ኪዳናዊ ኤርምያስ!" ብለው መኾኑን እንዲያውቁት ይኹን! ከዚህ እንዲያልፍ ቢያደርጉ እንኳ፡ በአገልግሎት መታወቂያዬ፡ "ንቡረ-እድ" ካሉኝ፡ ይበቃል።

"በመጨረሻ፡ 'አልፋ ወኦ፡ እኔ ነኝ!' ያለና በእኒሁ ሕያዋን አሌፉቱ አማካይነት፡ ይኸው አገናኝቶን የሚያነጋግረን፡ አምላከ ኢትዮጵያ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ከረዥም ዘመን በፊት፡ መልእክቷ ደርሶኝ፡ ዕድሜዬን ሙሉ ከማገለግላት መመኪያችን ቅድስት ድንግል እናቱ ጋር፡ እነርሱ በወሰኑት፡ በቅርቡ ኾነ በሩቁ ጊዜያቸው፡ በዓይነ ሥጋ ሊያስተያዩን እንደማይሳናቸው የታመነ ነው።"

**የአባ ዳንኤል ተጫኔ ደብዳቤ፡-**

በ. *"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን። ይድረስ እጅግ ለማከብርዎት ለምናፈክዎትም አባት ንቡረ እድ ኤርምያስ አባቴ አሁን ይህችን አጭር መልእክት የጻፍኩልዎት በጉም እየሱስ ገዳም እንዳከናውን የተሰጠኝን ስራ አከናውኔ አ/አ እደተመለስሁ ነው አባቴ አቋምዎት አልገባኝም የትነው ያሉ ለምንስ ወዳገርዎ ባስቸኮአይ አይገቡም ምላሽዎን ላኩልኝ እንዲህ ያልኩበት ከፍቅር ከናፍቆት ነው ብዙ የማይገቡኝን ምስጢራት በማየቴ እርስዎ በመንፈስ ቅዱስ ያልዎትን ቦታ ማወቄ ስውራን አብዝተው ሲሳሱሎዎ ማየቴ አሁን ደግሞ እርስዎ ለዘመናት የደከሙለት እውነት አፍርቶ የኢትዮጵያ ስውራን ሁሉ በታላቅ ግስጋሴ ላይ መሆናቸውን ባይኔ አይቸ ዳሰሸ ሰአታት እንደቀሩን አውቄ እለት እለት ልናገረው ያልተፈቀዱ ምስጢራትን አውቄ ነው እባክዎ አባቴ ደካማነቴን አይናቁት እሺ በሉኝ ወዳገርዎ ግቡ ቅዱሳንም አያስቸግሩ!*

*"ማለቴ ለእውነት የደከሙትን እያሰቡ ስለርስዎ የሚያደርጉትን ያየው አይኔ ያውቃል እኔም አብዝቸ ናፈኩዎ በተረፈ በዚህ የማልገልጣቸው ብዙ ምስጢራት አሉ በሚወዱአት ድንግል በስቸኩዋይ ወዳገርዎ ኑልን:: በተረፈ የሰጡኝን መጸሀፍ ሁሉ በነጻ እንደሰጡኝ ብዙ ሰው እንዲዲንበት በቤተ ክርስቲያን ቤተ መጻሀፍት በክበር ተቀምጦ ብዙዎች እየዳኑበት ነው በነጻ ሰው እንዲዲንበት እንደሰጡኝ እኔም ሳልሳሳ በነጻ ብዙዎት እንዲያገኙት ሰጥቻለሁ በእውነትም ብዙዎች እየዳኑበት ነው ማረጋገጥ ከፈለጉ ሰሜን ሸዋ ዞን መሀል ሜዳ ከተማ ቅዱስ ሚካኤል ደብር ሰንበት ተ/ቤት ቤተ መጻሀፍት ተረክቦት ብዙዎች እንደዳኑበት ምስክርነት ያገኛሉ እኔም አደራየን በመዋጣቴ ደስ ብሎኛል፤ የሰጡኝን ወርቅ አልቀበርኩም። ልጅዎ አባ ወልደ አረጋዊ (ዳንኤል ተጫነ)"*

<u>የእኔ መልስ፡-</u>

ይድረስ ለተወደዱና ለተከበሩ አባ ወልደ አረጋዊ! ደኅንነትዎን ያሳወቀኝ እ-ጦማርዎ ደረሰኝ፤ አስበው ስለጻፉልኝና በውስጡም ስላሠፈሯቸው መልካካም ቃላት፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ! የሚያካኺዱት የመንፈስ ቅዱስ ተልእኮዎ ስለተሳካልዎ፡ ኹላችንንም ደስ ያሰኛል፤ ለኹሉ ዋጋውን የማያስቀሩ፡ የሚያገለግሏቸው ቸሩ እግዚአብሔር፥ እናት አገራችንና መንግሥቱ የኾነችው እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ የአገልግሎትዎን ዋጋ እንደሚከፍሉዎ እሙን ነው።

ስላቀረቡልኝ ጥያቄና ስለሳሰቡኝ ቍም ነገር የምሰጥዎ መልስ ቢኖር፡ እንደሚከተለው ነው፡- ማናቸውም፡ የሚደርሰውና የሚኾነው፥ የሚፈጸመውም ኹሉ፡ መልካሙን ኹሉ በወጠኑ፥ እያካኼዱ ባሉትና በሚያከናውኑት፡ በእነርሱ፡ በቅድስቲቱ እናትና በተወደጁ ልጇ በተዘጋጀው መለኮታዊ ዕቅድ መሠረት ብቻ ስለኾነ፥ ለፍጥረተ ዓለሙም ኹሉ፡ የሚሻለውና የሚበጀው፡ ያ ነውና፡ እኔም፡ አኹን፡ "ለኹሉም፡ የእነርሱ ፈቃድ ይኹን!" እላለሁ።

የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ የእናታችን ኢትዮጵያ አገልጋዮች የኾንነው፡ እኔም ኾንሁ፥ እርስዎ፥ ሌሎቻችንም ኹሉ፡ እነርሱ፡ ለአገልግሎት ሲጠሩን፡ "አቤት! እመት!"፥ ሲልኩንም፡ "ወዴት!" ብለን፡ ፈቃዳቸውን፡ ያለውልውል፡ በቍርጥ ታማኝነት ለመፈጸም፡ ምንጊዜም፡ ፍጹም ዝግጁዎች ኾነን የምንጠባበቅ፡ ትሑታንና ታዛዦች ካህናት መኾናችን የታወቀ ነው፤ በዚህ ረገድ፡ አኹንም፡ በእኔ በኩል፡ ምንም ዓይነት ችግር የለምና፡ ኹሉም፡ እነርሱ በወሰኑት ጊዜ እንደሚፈጸም ላረጋግጥልዎ፥ ሌሎቻችንም፡ ይኸው፡ "የኢትዮጵያ ቀን" የተባለው፡ እግዚአብሔራዊ ጊዜ እስኪደርስ፡ በትዕግሥት መጠባበቅ እንዳለብን፡ ላዘክርዎ እወድዳለሁ።

እንግዴህ፡ ያ ኹሉ ውትወታ፡ ለዚሁ፡ ኤልያሳዊ ዓላማችሁ ስኬት እንዲያገለግል የታቀደ እንደነበረ፡ ሴራው፡ ይኸው፡ ከረቂቅ ወጥመዳችሁ ጋር፡ ተጋልጦ ቀረበ!

ነገር ግን፡ ቸሩ እግዚአብሔር፡ በቅዱስ መንፈሱ፥ እመቤታችን፡ ድንግል ማርያምም፡ በእናትነት ረድኤቷ፡ ከዚያ ወጥመድ ጠብቀው አዳኑኝ፤ ፍጹም ምስጋናዬ ይድረሳቸውና።

እኔማ፡ ምንጊዜም ሳደርገው እንደኖርሁት ኹሉ፡ በውጭ ያለውን አገልግሎቴን በሚመለከት፡ ቀደም ብዬ፡ አዘጋጅቼው የነበረውን ዓላማና ተግባር ፈጽሜ፡ ወደአገሬ በመመለስ፡ በዚያ የተገኘሁ መኾኔን፡ በዚህ አጋጣሚ፡ ስገልጽልዎ ደስ ይለኛል።

ለነገሩማ፡ "ኢትዮጵያ" ብለን የምንጠራትና የምናውቃት አገራችን፡ የአምላክ እናት፡ ድንግል ማርያም በመኾኗ፥ እርሷም፡ የሰማይና የምድር ንግሥት በመኾኗ፡ ፍጥረታተ ዓለማቱ ኹሉ፡ የእርሷ በመኾናቸው፡ መላው ዓለም፡ "ኢትዮጵያ" ከመኾኑ የተነሣ፡ አህጉራቱ ኹሉ፡ አገራችን መኾኑን ሊያውቁት የሚገባ የእግዚአብሔር እውነታ ነው።

፬ተኛ፡ አኹን ደግሞ፡ በመጨረሻው የነቀፌታ መልስዎ ያሉትን፡ መመልከት ነው፡-

*"ይህን ምስኪን የሚሄድበት አጥቶ በዕንባ ፈጣሪውን እየተማፀነ የሚገኘውን ሕዝብ አታወናብዱት፡፡ ሕይወቱን አታጨልሙበት፡፡ ስለእውነት ቁሙ! የኢትዮጵያ ጠላቶች በሆኑ በባዕዳን ሀገራት ተደብቃችሁ ግራ አታጋቡት፡፡ ግቡ ወደ አገራችሁ፡፡ ተዋሕዶን ፣ አንዷቷን ዕለተ ሰንበትንና ሕግ እና ነቢያትን አውጁ፡፡ከሚራበው ወገናችሁ ጋር ተራቡ፡፡ ከሚያለቅሰው ወገናችሁ ጋር አልቅሱ፡፡ ይህ ነው ኢትዮጵዊነት፡፡ ባሕር ማዶ መሽጎ ማውራት አይደለም፡፡"*

አዩ! ይህን የመሰለውን፡ የግብዝነትና የሽንገላ ቃላት በመናገርና በመጻፍ፡ ከእንግዴህ ወዲህ፡ እንኳንስ፡ ኹሉን አውቆ፡ ጽንፍ በሌለው ትዕግሥቱ፡ የፍጡሩን ክፋት የሚያሳልፈውን እግዚአብሔርን ይቅርና፡ ደካሞች ሰዎችን እንኳ ማወናበድ ከማይቻልበት ዘመን ተደርሷል።

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ለመንፈሳዊው ፍጥረተ ዓለም ብቻ ሳይኾን፡ ለግዙፉ ሥጋዊ ፍጥረተ ዓለም ጭምር፡ ራሷንና መሪዎች ባለቤቶቿ የኾኑትን፡ ንግሥቲቱን፡ የአምላክ እናት ድንግል ማርያምን እና ልጇን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በይፋ ዐዋጇ አማካይነት፡ ግልጽ አድርጋ አሳውቃለች።

እንግዴህ፡ "ዓይን አለኝ!" ለሚል ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ በሥነ ፍጥረቷና በዘመኑ ድርጊቶች አማካይነት፡ እርሷንና መሪዎቿን፡ እንዲያይ አድርጋለች። "ጆሮ አለኝ!" ለሚለውም ኹሉ፡ ቃሎቿን፡ በጎዋ ነጋሪት ሳይቀር፡ እያሰማች ትገኛለች። "አእምሮ አለኝ!" ለሚለውም፡ በአንክሮ በተዘክሮ አስተውሎ፡ በተፈጥሮው ጸጋ ወደተሰጠው፡ ወደእግዚአብሔራዊው እውቀቱ የሚመለስባቸውን ዕፁብ ድንቅ የእውነት መልእክቶቿን ማስተላልፏን ቀጥላለች።

እኔ፡ በጋብቻ ትዳር ተወስኜ፡ የእግዚአብሔር ፍሬዎችን አግኝቼ የምኖር ስኾን፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ከሕፃንነቴ ጀምሮ ሳካኼደው የኖርሁትን ተልእኮዬን ለመፈጸም፡ በአገር ቤትና በመላው ዓለም አህጉር መዘዋወሬ፡ ኢትዮጵያ፡ መላው ፍጥረተ ዓለም መኾኗን በማመን ነው። ከተወለድሁባት፥ ካደግሁባትና ካገለገልሁባት፥ በመጨረሻም፡ የመከራ አክሊልን ከተቀዳጀሁባት ምድር፥ ወደባሕር ማዶ፡ በፈቃድ ስደተኛነት የወጣሁት፡ ተልእኮየን በመቀጠል፡ ይህችኑ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን፡ ኢትዮጵያ አገሬንና ልጆቿ የኾኑትን ወገኖቼን ለማገልገል እንጂ፡ እንደእርስዎ አባባል፡ *"በባሕር ማዶ፡ መሸጎ ለማውራት"* አይደለም። ይህንኑ የተጠመድሁበትን አገልግሎቴን፡ ከነፍሬዎቹ፡ እርስዎ ጭምር ያውቁታል።

እኔን፡ እንዲህ ሲነቅፉ፡ እርስዎና እርስዎን የመሰሉት መነኰሳት፡ ምን እያደረጋችሁ እንደኾነ ተገንዝበውታል? የምንኵስና ሥርዓታችሁ የሚያዝዘው፡ ምን እንደኾነስ ያውቁታል? የዓለማውያኑ ሰዎች መኖሪያ ከኾነው፡ ከከተማ ወጥታችሁና ተለይታችሁ፥ ርቃችሁም፡ በገዳም፡ ማለትም፡ በበረሃ ተወስናችሁ እንድትቀመጡ ሲኾን፡ በይፋ እያደረጋችሁ ያላችሁትን ግብር ግን፡ ራስዎን ጭምር፡ እስኪ ይመልከቱ! አዎን! ምን እያደረጋችሁ ነው?

ከዚሁ ሥርዓታችሁ ውጪ፡ በአገር ቤትም ኾነ፡ በባሕር ማዶ በሚገኙት፡ ከተሞች ውስጥ፡ በተድላ ደስታ ምቾት መኖር ብቻ አይደለም፤ በዚያ እየኖሩ፡ በሥነ ምግባር ውርደትና በፍትወተ ሥጋ ውድቀት ምክንያት፡ ለማኅበረ ሰቡ፡ ክፉ አርአያ መኾንም ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን፡ ሥርዓታችሁ፡ እጅግ አድርጎ በሚያወግዘው፡ በገንዘብና በሥልጣን ስስት ምክንያት፥ ከዚህም በላይ፡ ቤትና ንብረትን በማካበት ጭምር፡ በየግላችሁና እርስ በርሳችሁ በምታካኺዱትና በምታራምዱት፡ እጅግ በነደደው የፀብና የመለያየት ሰልፋችሁ፡ ምን ዓይነቱን የጥፋት ምልክት እያሳያችሁ እንደኾናችሁ፡ ያወቃችሁ ይመስልዎታል!? "ይኼ ኹኔታችሁ፡ ጤናማ ምልክት ነው!" ይላሉ?

ለኹሉ፡ እንደየሥራው የሚከፍለው፡ እውነተኛው ዳኛ ስላለ፡ ፍርዱን ለእርሱ እንተወውና፡ ስለእኔ ለተናገሩት የነቀፌታ ወቀሳ፡ ራሴን ለመከላከል፥ ወይም፡ ስለራሴ ልመጻደቅ ሳይኾን፡ አንባቢዎቻችንን፡ ካለማወቅ ስሕተት ለማዳን ብቻ ስል፡ የምገልጸው እውነታ ቢኖር፡ ይህ ነው፦

ጌታችን ኢየሱስ መሢሕ፡ **"አንትሙሰ፡ ኅሡ መቅድመ፡ መንግሥቶ፥ ወጽድቆ፤ ወዝንቱሰ ኵሉ ይትዌሰከክሙ።"**

ማለትም፡ **"እናንተ ግን፡ አስቀድማችሁ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት፥ እውነቱንም ፈልጉ! ይህ ኹሉ ይጨመርላችኋል።"** ሲል የተናገረውን መለኮታዊ ቃሉን አምኜ በመከተል፡ ካገለገልሁባቸው፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ምልክናና ቤተ ክህነት፡ አንዳችም የጡረታ አበልን እንኳ ሳልቀበል፥ ሳልጠይቅም፡ እርሱ፡ ቸሩ ፈጣሪ፡ **"በከንቱ ዘነሣእክሙ፡ በከንቱ ሀቡ! በጸጋ ዘነሣእክሙ፡ በጸጋ ሀቡ!"**

ማለትም፡ "ከእኔ፡ ኹሉን፡ እንዲሁ፡ በልግሥና ያገኛችሁ ስለኾነ፡ እናንተም፡ ኹሉን፡ እንዲሁ፡ በልግሥና ስጡ!" ባለው መለኮታዊ መመሪያው መሠረት፡ በሥነ ተፈጥሮ በሰጠኝ ሙሉ አካልና ጤንነት በመጠቀም፡ የጉልበት ሥራን እየሠራሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ እውነቱንና መንግሥቱ የኾነችውን እናቱን ድንግል ማርያም ኢትዮጵያን፡ በነፃ የማገለግል ኢትዮጵያዊ ነኝ፡ እኔ። (ማቴ. ፲፥ ፴፫። ፲፥ ፱)

ከዚህ ጋር፥ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት፡ ባልተቤቴና እኔ፡ የዛሬ ስድሳ ዓመት እንደተጋባን፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለአገልግሎት ተቀጥረን ከምናገኘው የወር ደመወዝ፡ በከፈልነው፡ በቤተ ንዋይ የገንዘብ ብድር፡ ዕቃዎቹ ጭምር ተሟልተው፡ በአዲስ አበባ፡ በሠራነው የጭቃ ቤታችን፡ እስከዛሬ፡ ከነቤተሰቤ ያለችግር፡ በሰላም ከመኖር በቀር፡ ሌላ የማውቀው፥ የኾነም ነገር፡ ከቶ የለም።

በመጨረሻ፡ ከተለመደው ጸሎታችን ጋር፡ ለእርስዎ፡ ለአባ ዳንኤል ተጫነ አግዜና ለመሰሎችዎ ኹሉ፡ እንደገና የማሳስበው፡ ወደአማናዊው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ማንነታችሁ፡ በእውነተኛው ንስሓ እንድትመለሱ ነው።

*[ከዚህ ጋር የተያያዘውንና የቀረውን የደብዳቤ ልውውጥ፡ በነዋ ሰሌዳችንና በፌስቡክ መዛግብታችን ውስጥ ለምንባብ ተቀምጠው ታገኛቸዋለህ።]*

<u>ኹለተኛው</u> ደግሞ፡ ይህ ነው፡- እርሱም፡ ኢትዮጵያ የኾነችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የዛሬ አገልጋይዋን ኤርምያስን በሚመለከት፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፤ በስድስተኛው የቃለ-ዐዋዲ ዐዋጅ፡ ከተናገረችው ውስጥ "አግባብነት ያለው ተጠቃሽ ክፍል" የተባለው ነው።

«ልጇ ወዳጇ፡ "**መነ ይብልዎ ሰብእ፡ ለወልደ ዕጓለ እመሕያው? እኔን፡ የማርያምን ልጅ፡ ሰዎች፡ ማን ይሉኛል?**" ብሎ፡ ሓዋርያቱን በጠየቃቸው ጊዜ፡ "**ወይቤልዎ፡ 'ቦ፡ እለ ይብሉከ፡ ‹ዮሓንስሃ መጥምቀ!›፤ ወካልአን፡ ‹ኤልያስሃ!›፤ ወመንፈቆሙ፡ ‹ኤርምያስሃ!›፤ ወእመአኮ፡ ‹አሓዱ እምነቢያት ቀደምት!›።**

**«‹መጥምቁ ዮሓንስ ነው!›፥ ሌሎችም፡ ‹ኤልያስ ነው!›፥ እኩሌቶቹም፡ ‹ኤርምያስ ነው!›፥ ያም ባይኾን፡ ‹ከቀደሙት ነቢያት አንዱ ነህ!" የሚሉህ አሉ፤' አሉት።"**

«እንግዲህ፡ ሓዋርያቱ፡ በዚህ መልሳቸው ውስጥ፡ በስም ለይተው የጠቀሷቸው ነቢያት፡ መጥምቁ ዮሓንስ፥ ኤልያስና ኤርምያስ ሲኾኑ፡ በጊዜው፡ በአካለ ሥጋ፡ ዐብሮአቸው የነበረው መጥምቁ ዮሓንስ፡ በኤልያስ መንፈስ የመጣ መኾኑን፡ ልጇ ወዳጇ፡ "**ወእመሰ ትፈቅዱ ትትወከፍዎ፡ ዝ ውእቱ ኤልያስ፡ ዘሀለዎ ይምጻእ፤ ዘቦ ዕዝን፡ ሰሚዐ ለይስማዕ!**

"ልትቀበሉትስ ብትወድዱ፡ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ፡ ይህ ነው። የሚሰማ ጆሮ ያለው፡ ይስማ!" እንዳላቸው ታውቃላችሁ።

«ከዚያ በኋላም፡ በደብረ ታቦር ላይ፡ ኤልያስን፡ ከሙሴ ጋር አይተውት፡ ከተራራው ሲወርዱ፡ "እፎ ይብሉ ጸሓፍት፡ 'ሀለዎ ይምጻእ ኤልያስ ቅድመ'።"

"እንግዲህ፡ ጻፎች! 'ኤልያስ፡ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል!' ስለምን ይላሉ?" ብለው በጠየቁት ጊዜ፡ ልጇ ወዳጇ፡ መልሶ፡ "እወ! ኤልያስ፡ ይቀድም መጺአ፤ ወያስተራትዕ ኵሎ። ወእብለክሙ ባሕቱ፡ ከመ ኤልያስ፡ ወድአ መጽአ፤ ወኢያእመርዎ፤ ወባሕቱ፡ ገብሩ ላዕሌሁ፡ ኵሎ፡ ዘከመ ፈቀዱ።

"ኤልያስማ፡ አስቀድሞ ይመጣል፤ ኹሉንም ያቀናል፤ ነገር ግን፡ እላችኋለሁ፦ <u>ኤልያስ፡ ከዚህ በፊት መጣ፤ የወደዱትንም ኹሉ አደረጉበት እንጂ፡ አላወቁትም።</u>" አላቸው። (ማቴ. ፲፩፥ ፲፬፤ ፲፯፥ ፩-፲፫።)

«ስለዚህ፡ የእኔ ልጆች በኾኑት፡ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ ሳይኾን፡ "የእስራኤል ልጆች ነን!" በሚሉት፡ በዛሬዎቹ አይሁድ ዘንድ፡ "ይመጣል!" ተብሎ፡ ገና የሚጠበቀው፡ ነቢይ፡ ኤርምያስ ከኾነ፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ እነርሱና የእነርሱን ፈለግ በምትከተሉት፡ በባለሦስት ሺ ዓመታቱ ኦሪታውያን ዘንድ፡ መጥምቁ ዮሓንስ፡ በኤልያስ መንፈስ እንደመጣ ኹሉ፡ ይኼ የዛሬው አገልጋያችን ኤርምያስም፡ ባታምኑበት እንኳ፡ "ምናልባት፡ በዚያ፡ በቀደመው ኢትዮጵያዊ ነቢይ ኤርምያስ መንፈስ የመጣ ሊኾን ይችል ይኾናል!" ብላችሁ፡ በጥርጣሬና በማመንታትም ቢኾን፡ ተቀብላችሁ ልትሰሙት፡ ለምን አልቻላችሁም?

«"አቤሜሌክና ባሮክ" የተባሉ፡ ኢትዮጵያውያን ደቀ መዛሙርት የነበሩትን፡ ያን ታላቁን፡ የብሉዩን ዘመን፡ ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስን፡ በዘመኑ የነበሩት ከሃዲዎች፥ ዓመፀኞና አመንዝሮች አይሁድ እንዳልተቀበሉት ኹሉ፡ እናንተም የዛሬዎቹ ተከታዮቻቸው፡ የዛሬውን አገልጋያችንን ኤርምያስን፡ "አንቀበልህም! አንሰማህም!" ማለታችሁ አይደለምን?

«እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! እነዚያ የቀደሙት መሰሎቻችሁ፡ እጅግ ተጎዱ እንጂ፡ ምን ተጠቀሙ? ያ ነቢያችን፡ በትንቢታዊ ቃሉ ያላቸውና የነገራቸው፥ በጽሕፈትም የላከላቸው ምክርና ማስጠንቀቂያ፡ አንድ ሳይቀር፡ እንደደረሰባቸውና እንደተፈጸመባቸው፡ ኹላችሁ የምታውቁት ዝክረ ነገር ነው። የዛሬዎቹ፡ እናንተስ፡ ምን እያደረጋችሁ ነው? ይህ የዛሬው አገልጋያችን፡ ወደእናንተ እያደረሰ ያለውን መልእክታችንን ተቀብላችሁ ባለመስማታችሁ፡ ምን እየደረሰባችሁ እንደኾነ፡ ይኸው፡ ለአርባ ዓመታት አያችሁት አይደለምን? ለወደፊትስ፡ የሚጠብቃችሁ ምን እንደኾነ ለማወቅ፡ ካለፋችሁበት ፈተናና መከራ፥ ሥቃይና ዋይታ መማር ያዳግታችኋልን? አያዳግታችሁም።

«ይህ አድራጎታችሁ፡ አኹንም፡ እንደእንግዳ ነገር ተቆጥሮ፡ የሚያስገርም ሊኾን እንደማይችል የታመነ ነው። ምክንያቱም፡ ያ የቀደመው፡ ኢትዮጵያዊው ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ፡ ወገኖቹን፡ ከታላቅ ውድቀትና ጥፋት ለማዳን ሲል፡ የተቃዋሚዎቹን ያልተቋረጠ ዛቻና ጥቃት ሳይፈራና ሳይሠቀቅ፡ መልእክታችንን፡ ለሕዝቡና ለአለቆቹ ባለመሰልቸት ያደርስ በነበረበት ጊዜ፡ በእርሱ በኩል፡ በሚበቃ ተናግሮና መክሮ፥ ተማጽኖና አስጠንቅቆ እንደነበረ፥ በእነርሱ በኩል ግን እንዳልሰሙትና እንዳልተቀበሉት ዜና መዋዕሉ ስለሚዘክር ነው።

«አዎን! ከኢዮስያስ ዘመን አንሥቶ፡ እስከ ኢዮአቄም፥ ከዚያም፡ በመጨረሻ፡ የባቢሎን ምርኮ እስከኾነበት፡ እስከሴዴቅያስ ዘመን ድረስ፡ በኢየሩሳሌም በነበሩት፡ በይሁዳ ነገሥታት አገዛዝ ሥር ይመሩና ይተዳደሩ የነበሩት፡ "አይሁድ" የተባሉት፡ የእስራኤል ልጆች፡ ጽዋቸው፡ በባቢሎኑ ንጉሥ፡ በናቡከደነፆር አስፈሪ ሠራዊትና የጭካኔ ሰይፍ እጅ ወድቆ ማለቅ፥ ፈራርሶ መቅረትና በምርኮ መወሰድ እንደሚኾን፡ የዚያ፡ የቀደመው ነቢያችን ዝክረ ነገር በተነሣ ቁጥር፡ ይህ ርእሰ ነገር፡ በእየጊዜው ሲወሳ ይኖራል።

«ያን የመሰለው ጽዋ፡ የእነዚያ አይሁድ ዕድል ፋንታ የኾነው፡ እግዚአብሔር፡ ከአብርሃም፥ ከይስሓቅና ከያዕቆብ፥ ከእነርሱም በኋላ፡ ከሙሴና ከዳዊት ጋር የተካየዳቸውን ሦስት ኪዳናት፡ በክህደትና በዐመፅ፥ በአምልኮ አመንዝራነትና በልዩ ልዩ የክፋት ሥራ ፈጽመው በማፍረሳቸው፥ ከዚህም የኃጢአት አካኼዳቸው፡ በንስሓ ለመመለስ፡ ምንም ዓይነት፡ የበጎ ፈቃድ ዝንባሌን ሊያሳዩ ባለመቻላቸው እንደነበረም ተነግሩዋል።

«እንደዚሁ ኹሉ፡ የዚያን ነቢየ እግዚአብሔር ስም ብቻ ሳይኾን፡ ፈለጉንም የተከተለው፡ የዚህ ዘመን የተልእኮ አገልጋያችን ኤርምያስ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚለው ኹነ፡ ከዚህ ውጭ ላለው፡ ለዚህ፡ ለዛሬው፡ የፍጥረተ ዓለሙ ትውልድ ያደረሰውን፡ የምሕረት መልእክታችንን፡ ይኸው ትውልድ፡ ሰምቶና ተቀብሎ፡ ምርጫው፡ በእውነተኛ ንስሓ ለመመለስ ሳይኾን ቀረ። እንዲያውም፡ ዓላማና ተግባሩ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ ለአርባ ዓመታት፡ በገሃድና በይፋ ሲያካኺድ የኖረውን፡ የክህደትና የዐመፅ፥ የአምልኮ አመንዝራነትና የልዩ ልዩ የክፋት ሥራ፡ አኹንም መቀጠል ኾኖ ተገኘ።

«ከዚህ የተነሣ፡ ይኸው ትውልድ፡ ተደጋግሞ እንደተነገረው፡ ራሱን፡ በእውነተኛው ንስሓ ካልመለሰና አካኼዱን ካላስተካከለ በቀር፡ ዕድል ፋንታው፡ በኢየሩሳሌም በነበሩት፡ "አይሁድ" በተባሉት፡ በእስራኤል ልጆች የተጨለጠውን፡ የባቢሎንን መራራ ጽዋን የመሰለ ፍጻሜ እንደሚጠብቀው በማስገንዘብ፡ እነሆ፡ አገልጋያችን ኤርምያስ፡ ከሕፃንነቱ ጀምሮ የተጠራበትን ተልእኮ፡ በበኩሉ መፈጸሙን አስታውቆን፡ ከእኛ የተቀበለውን፡ ኃላፊነቱንና አደራውን አስረክቦናል።

«አዎን! ይኸው፡ ኢትዮጵያዊው አገልጋያችን ኤርምያስ፡ እንዲህ፡ በኃላፊነትና በአደራ፡ ከእኛ የተሰጠውን ተልእኮ፡ ባለው ዓቅሙ፡ ከዚህ፡ አኹን ከሚገኝበት ምዕራፍ አድርሷል። ከእኛ የተሰጠውን፡ ይህንኑ ኃላፊነትና አደራም፡ ለእኛ አስረክቦናል። እኛም፡ መርቀን ተረክበነዋል። ከዚህ በኋላ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን፡ ልጄ ወዳጄና እኔ፤ እኛው ራሳችን፡ ስንመራትና ስናስተዳድራት፥ ስንጠብቃትና ስንቈጣጠራት እንደኖርን ኹሉ፡ አኹንና ወደፊትም፡ ይኸው አያያዝና አሠራር፥ አካኼድና አፈጻጸም፡ በዚሁ መልኩና ይዘቱ የሚቀጥል ይኾናል።

«በእርሱ አማካይነት ስናስተላልፍላችሁ የቆየውንም የምሥራች መልእክታችንን፡ ልጄ ወዳጄና እኔ፤ ራሳችን፡ እንዲህ፡ በቀጥታ የምናሰማችሁ ኾኖ፡ ዝግጅቱና አቀራረቡ ግን፡ አኹንና ወደፊት፡ እንደተለመደው፡ በእርሱው፡ በኤርምያስ አገልጋይነትና አማካይነት የሚካኼድ ይኾናል።

«እንዲያ ባይኾንማ፡ ዛሬ እኛ፡ እናንተን፡ እንዲህ፡ በቀጥታ ልናናግራችሁና ልንመክራችሁ፥ ልንወቅሳችሁና ልናስጠነቅቃችሁ፡ እንደምን ይቻለን ነበር? አያመቸንም ነበር።»

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምንባቦች እንደሚያረጋግጡት፡ መቼም **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ከተመሠረተችበት ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥታ፡ ይኸው እንግዴህ፡ እስካኹን፡ ለ፯ሺ፭፻፰ ዓመታት ተጠብቃ፡ ስትመራና ስትካኼድ የኖረችው፥ አኹንም እየተመራችና እየተካኼደች ያለችው፥ ወደፊትም፡ ስትመራና ስትካኼድ የምትኖረው፡ በቅድስት ሥላሴ መለኮታዊ ፈጣሪነቷና ባለቤትነቷ፡ ማለትም፡ በራሱ፡ በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ፡ ይኸውም፡ በእግዚአብሔር ንጉሥነትና ክህነት፥ በድንግል ማርያምም ንግሥትነትና ሃይማኖትነት መኾኑን ታውቀዋለህ።

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! እያንዳንዳችን፡ ኢትዮጵያውያን ኪዳናውያንና ኢትዮጵያውያት ኪዳናውያት፡ ይኸው አኹን፡ አንተም በበኩልህ እንደምታደርገው ኹሉ፡ በየፊናችን የምናበረክተውን፡ የየግል አገልግሎታችንን፡ በያለንበት ከመቀጠል በቀር፡ በዚህ ድርጅት ኾነ፡ በሌሎቹ ተመሳሳይ ፀረ-እግዚአብሔርና ፀረ-ኢትዮጵያ በኾኑት ሰብአውያን ተቋሞች በኩል፡ በዚችው፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ላይ፡ እየተካኼደ ያለው፡ ይህን የመሰለው እኩይ ተግባር፡ በምንም መንገድ፡ ፈጽሞ የሚያሳስበን ሊኾን አይችልም። ቅንጣት የምታህል ጉዳትን ሊያስከትሉባት ስለማይችሉ ነው።

ከፉዎች፡ በገዛ ሥራቸው፡ እየራሳቸውን ሲጎዱና ሲያጠፉ እያየን ከምናዝንና ከምንደነቅ በቀር፡ በእርሷ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ላይ፡ ኢምንት ጥቃትን ሊያደርሱ፡ አንዳችም ዓቅም እንደሌላቸውማ፡ ይኸው በተፈጥሮው ሥርዓት ጽናት እያየነው አይደለምን?

አዎን! በእርሷ ፈጣሪነት የተገኙት፥ በእርሷም ባለቤትነት፡ የሚጠበቁትና የሚመሩት፡ የሰማያቱና የምድሪቱ፡ ፍጥረታተ ዓለማት፡ በየህልውናቸውና በየኺደታቸው የተፈጥሮ ሥርዓታቸው ላይ፡ ምንም ዓይነት እንከንና ለውጥ፥ ሁከትና ነውጥ፡ ፈጽሞ ሳይደርስባቸውና ሳይከሠትባቸው፡ በፍጹም ጽሙናና ጸጥታ፡ ከታማኞች ሕያዋን ፍጡሮቻቸው ጋር፡ በሕይወት ሲጓዙ፡ ይኸው እንመለከታለን፤ ለቅዱሱ ኪዳን አምላካችን፡ ምስጋናችን ይድረሰውና።

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እኮ፡ ለፍጥረቶቿ ኹሉ፡ የሚያስፈልገውን ታደርጋለች እንጂ፡ ለእርሷ፡ የማንም ፍጡር፥ የእኛ የኪዳናውያንና ኪዳናውያት ጭምር፡ አገልግሎት፥ እርዳታና እገዛም፡ ከቶ አያስፈልጋትም። እኛ፡ እያንዳንዳችንም ብንኾን፡ እንዲህ፡ በእየራሳችን ሕዝባዊ፥ መለካዊና ክህነታዊ ተልእኳችን ለመጠመድ የበቃነው፡ ለእርሷ ካለን ጽኑ ፍቅር የተነሣ፡ መለኮታዊዉን የደስታና የበረከት ሕይወት፡ በገዛ ፍላጎታችንና ፈቃዳችን ለመሳተፍ ስንል መኾኑ፡ በኹላችንም ዘንድ የታወቀና የታመነበት እውነታ ነው።

ስለዚህ፡ በዚህ ረገድ፡ በእኔ በኩል ላደርገው ስለሚገባኝ ኪዳናዊ ተልእኮ፡ እንዳንተ፥ እንደሌሎቹም ኪዳናውያትና ኪዳናውያን ኹሉ፡ እኔም፡ ቃል ኪዳን የገባሁበትን ተግባር፡ በተቻለኝ ዓቅም፡ አሟልቼ ለመፈጸም ከመትጋት፡ ወደኋላ እንደማልል እያረጋገጥሁልህ፡ በአንተ በኩል፡ አስበህ ስላደረግኸው፡ ስለዚህ ኪዳናዊ ድርሻህ፡ እንደገና፡ "እግዜር ይስጥልኝ!" እልሃለሁ።

በዚህ ጉዳይ ላይ፡ የጻፍህልኝን ደብዳቤና ዐባሪዎቹን ጭምር፡ የአገልግሎት ባልደረቦቻችን የኾኑት ኪዳናውያት እኅቶቻችንና ኪዳናውያን ወንድሞቻችን ቢመለከቷቸው፡ የሚጠቅሟቸው መስለው ስለታዩኝ፡ ከዚህ መልሴ ጋር፡ በማከታተል የምልክላቸው መኾኔን እንድታውቀው ይኹን!

ለኪዳናዊት እመቤት ወለተ-ጊዮርጊስ ሰላምታዬን በማቅረብ፥ በአደራ የተሰጧችሁን፡ ኪዳናውያትና ኪዳናዊ የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆችንም፡ ዐቅፊህ በመሳም፡ ፍቅሬንና ናፍቆቴን አሳውቅልኝ።

በያለንበት፡ የተቀደሰና የደስታ የዓውደ-ዓመት በዓልን እንድናከብር ላበቁን እግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ፡ ምስጋናችን ይድረሳቸው!

ኪዳናዊ ወንድምህ፡ ንቡረ-እድ ኤርምያስ።